DC | HEALTH
GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA

GOVERNMENT OF THE DISTRICT OF COLUMBIA
MURIEL BOWSER, MAYOR

# የደረጃ 1 መመሪያ

## ኮሮና ቫይረስ 2019(COVID-19): ለሬስቶራንቶች የሚሆን መመሪያ

በደረጃ 1 ወቅት ህዝቡ እና የተለያዩ ቢዝነሶች ለሁሉም የተጋላጭነት መጠን ቅነሳ ሲባል አዳዲስ ባህሪያትን እና ጠንከር ያሉ የመከላከያ ልማዶችን እንዲያዳብሩ ይጠየቃሉ። ይህ መመሪያ በደረጃ 1 ወቅት ለምግብ ተቋማቶች የታሰበ ነው :: አገልግሎቶችን የሚያቀርቡ ከሆነ፣ **በሠራተኞች ፣ በደንበኞች እና በማህበረሰቡ መካከል የ COVID-19 ስርጭትን ለመቀነስ ሲባል የሚከተሉትን እርምጃዎች መተግበር አለባቸው :: ለበለጠ መረጃ** coronavirus.dc.gov/phaseone **ን ይጎብኙ።**

### ለደንበኞች የሚሰጥ አትኩሮት

- ***የታመሙ እንደሆነ ወደ ሬስቶራንት አይሂዱ።:***
- አገልግሎቱ ከቤት ውጭ ለተቀመጡ ደንበኞች ብቻ የተገደበ ሲሆን እንዲሁም ጠረጴዛዎቹ አገልግሎት ለመስጠት ቢያንስ በ 6 ጫማ ርቀት ላይ ተቀምጠዋል። **ከቤት ውጭ ባለ ባር መቆም እና / ወይም መቀመጥ የተከለከለ ነው ::**
- ጠረጴዛዎቹ ለ 6 እና ከዛ በታች ለሆኑ ሰዎች የተገደቡ ናቸው።
- ቦታ ማስያዣዎች ይበረታታሉ እንዲሁም የመመገቢያ መረጃ መዝገቦች ቢያንስ ለ 30 ቀናት ይቀመጣል። ተጠቃሚዎቹ ስም እና የአድራሻ መረጃዎችን እንዲሁም የመድረሻ ጊዜን ማስመዝገብ አለባቸው።
- በማይበሉበትም ሆነ በማይጠጡበት ጊዜ የፊት መሸፈኛዎችን ይልበሱ (ለምሳሌ፡ ምግብ በሚታዘዙበት እና ምግብ ከመቅረቡ በፊት እና ከተጠናቀቀ በኋላ)፣ እናም በመደብዎ ውስጥ ከሌሉ ሰዎች የ 6 ጫማ ርቀት ያኑሩ ::

### ለሠራተኞች የሚሰጥ አትኩሮቶች

- ***የታመሙ ከሆነ ወደ ሥራ ለመግባት ሪፖርት አያድርጉ ::***
- መጸዳጃ ቤት ከመጠቀምዎ በፊት እና በኋላ ፣ ምግብ እና መጠጦች ከመቅረብዎ በፊት እንዲሁም ጥቅም ላይ የዋሉትን የምግብ ማሰናጃ እቃዎች ፣ የመስታወት ዕቃዎች ፣ የመብል መገልገያዎች እና ናፕኪኖችን ከጠረጴዛዎች ላይ ካስወገዱ በኃላ አዘውትረው እጆችዎን ይታጠቡ እንዲሁም በስራ ጊዜ ተገቢውን የፊት መሸፈኛዎችን ያድርጉ ::
- ሠራተኞች ለመበላት-ዝግጁ-የሆኑ ምግቦችን በሚያሰናዱበት ጊዜ ጓንት መልበስ አለባቸው ::
- በሚቻልበት ቦታ ሠራተኞች መሰብሰብን ለመከላከል እና የ 6 ጫማ ማህበራዊ የርቀት መመሪያዎችን ለመጠበቅ በአስተማማኝ ሁኔታ መመደብ አለባቸው ::
- በሥራ ቦታ በሠራተኞች መካከል ወይም ከደንበኞች ጋር የሚደረግ የእጅ መጨባበጥ እና ሌሎችም የሰው-ለሰው ግንኙነቶች የተከለከሉ ናቸው ::
- የሌሎች ሰራተኞችን ስልኮች ፣ ዴስኮች ፣ ቢሮዎች ወይም ሌሎች የስራ መሳሪያዎች እና ቁሳቁሶች (ለምሳሌ፡ እስክሪብቶ ፣ እርሳስ ፣ ቼክ መያዣ ፣ ወዘተ) ከመጠቀም ይቆጠቡ ::
- ሰራተኞች አብዛኛውን ጊዜ የሚነኳቸውን ወይም የሚጠቀሙባቸዉን ነገሮች (ለምሳሌ፡ የበር እጀታዎች ፣ የስራ ጣቢያዎች፣ ኮምፒዩተሮች) እና በአጠቃቀም ጊዜ የተጋሩዋቸውን ዕቃዎች እና ነገሮችን (ለምሳሌ ፣ የትእዛዝ እና የክፍያ ተርሚናሎች ፣ የጥሬ ገንዘብ መመዝገቢያ ወረቀቶች ፣ ጠረጴዛዎች፣ ካውንተርቶፕስ/ባር፣ የመቀበያ ትሪዎች) ቢያንስ በየአራት እና ስድስት ሰአታት ልዩነት ማፅዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ማድረግ።:
- አንድ ሠራተኛ ከታመመ ወይም ከ COVID-19 ጋር ተዛማች የሆኑ ምልክቶችን ማሳየት ከጀመረ ወዲያውኑ ሥራን በማቆም ፣ እነዚህን ምልክቶች ለአስተዳዳሪዎች ሪፖርት በማድረግ እና ለተጨማሪ ምርመራ የህክምና ባለሙያን የማነጋገር መመሪያን በመያዝ ከስራ ቦታ መውጣት አለባቸው ::

### ለአሰሪዎች የሚሰጥ አትኩሮት

- ሰራተኞች ስለ COVID-19 ምልክቶች እንዲሁም መሰረታዊ የመከላከያ እርምጃዎች መማር አለባቸው :: ለበለጠ መረጃ፣ coronavirus.dc.gov ን ይጎብኙ

- ሁሉንም ሠራተኞች ከታመሙ እና ተገቢ ከሆነ ክፍያ ጋር የዕረፍት ፈቃድ ከወሰዱ ወደ ሥራ መምጣት እንደሌለባቸው በጽሑፍ ያሳውቁ ። ተለዋዋጭ እና ቅጣትን የማያሳዩ የመልቀቂያ ፖሊሲዎችን ይተግብሩ ፣ እንዲሁም የታመሙ ሰራተኞች ቤት እንዲቆዩ ይፍቀዱ ።

- በፈረቃቸው መጀመሪያ ላይ፣ ወደ ተቋሙ ወይም ወደ ሥራው ከመግባታቸው በፊት በሰራተኞቹ ላይ የሚታዩትን ምልክቶች (ትኩሳትን ጨምሮ) በጥያቄ መልክ ይገምግሙ ። የታመሙ ሰራተኞች ለሥራ ሪፖርት ማድረግ የለባቸውም ።

- የሶስተኛ ወገን መልእክት አድራሽ አሽከርካሪዎች እና ማንኛውም አቅራቢዎች ስለ ማህበራዊ ርቀት ፣ የፊት መሸፈኛን ስለ ማድረግ እና ስለ የእጅ ንጽህና መስፈርቶች ማሳወቅ እና ማስታወስ ።

## የተቋም አተገባበሮች

- ማንም ትኩሳት ወይም የ COVID-19 ምልክት ያለው ሰው ወደ ተቋሙ እንዲገባ የማይፈቀድለት እና እነዚህም ግለሰቦች ጭምብል ወይም የፊት ሽፋን ማደረግ የሚጠበቅባቸው መሆኑን በመግለጽ ምልክቶችን መለጠፍ።
- የእጅ ማፅጃ ሳይኒታይዘር በተቋሙ እያንዳንዱ መግቢያ ላይ በቀላሉ መገኘት መቻል አለበት ።
- የሚቻል ከሆነ የተመሳሳይ አቅጣጫ የደንበኞች ፍሰትን ለማመቻቸት ለተቋሙ የተለየ መግቢያ እና መውጫ ያድርጉ
- መቀመጫ ለማግኘት በሚጠባበቁበት ጊዜ (ለምሳሌ ፣ የወለል ምልክቶች ፣ ከቤት ውጭ መዘግየት ፣ ወይም በመኪኖች ውስጥ እየጠበቁ) የደንበኞች ርቀትን ለማረጋገጥ ሂደቶችን መንደፍ እና መተግበር። ደንበኞች በመጠባበቂያ ስፍራዎች ወይም ባር አከባቢዎች እንዲሰባሰቡ አለመፍቀድ ።

- አገልግሎት እንዲሰጥ የሚፈቀደው ከቤት ውጭ ባሉ መቀመጫዎች ላይ ብቻ ነው
- የደንበኞችን በአካል መቀራረብ የሚጠይቁ እንቅስቃሴዎችን አለመፍቀድ ።
- ሊጣሉ የሚችሉ የወረቀት ሜኑዎችን መጠቀም በጥብቅ ይበረታታል ። እያንዳንዱ ደንበኛ ከተጠቀመ በኋላ የሚጣሉ የወረቀት ሜኑዎች መወገድ አለባቸው ። እንደገና ጥቅም ላይ የሚውሉ ሜኑዎችን የሚጠቀሙ ከሆነ ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኃላ መፀዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ መደረግ አለባቸው።

- ቡፌ ፣ በጥሬ የሚበሉ ምግቦች እና ሌሎች የጋራ መጠቀሚያ ስፍራዎች የተከለከሉ ናቸው ።
- ከግል አገልግሎት መስጫ ቦታዎች ለምሳሌ የመጠጥ ጣብያዎች ፣ የኮንዲመንት ጣቢያዎች፣ እና የመብል መገልገያዎች እና የናፕኪን ጣቢያዎች ዕቃዎች መወገድ አለባቸው፤ ይልቁንስ ሰራተኞችም እነዚህን ዕቃዎች በቀጥታ ለደንበኞች መስጠት አለባቸው ። ለአንዴ ብቻ ጥቅም ላይ የሚዉሉ ዕቃዎችን መጠቀም በጣም ይበረታታል ።

## ግንባታ አትኩሮቶች

- የቆሸሸ ውሃን ለማፅዳት እና በንጹህ ውሃ ለመተካት የውሃ ስርዓቶች እንዲታጠቡ ያድርጉ። ይህ ውሃው ውስጥ ሊገባ የሚችልን ማንኛውንም ብረት (ለምሳሌ፡ ሊድ) ያስወግዳል እንዲሁም ለ Legionnaires በሽታ እና ለሌሎች ከውኃ ጋር የተዛመዱ በሽታዎች ተጋላጭነት ይቀንሳል (https://www.cdc.gov/coronavirus/ 2019-ncov / php / building-water-system.html)

## ማጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ ማድረግ / ሳኒታይዜሽን

- ሁሉም የጠረጴዛ ዕቃዎች ለአንዴ ብቻ ጥቅም ላይ የሚዉሉ እና በኋላም የሚወገዱ ፣ ወይም በአጠቃቀም / ጠረጴዛ መቀመጫዎች ጊዜ መካከል መፅዳት እና ሰኒታይዝ መደረግ አለባቸው ። ይህ ዲጂታል የማዘዣ እስክሪኖች ፣ የመብል መገልገያዎች ፣ የመብል ማቅረቢያ ዕቃዎች ፣ የመጠጥ ማቅረቢያ ፣ የጠረጴዛ ልብሶች እና የናፕኪን እና የኮንዲመንት መያዣ እቃዎች (ማለትም በደንበኞች ሊነካ የሚችል ማንኛውም ዕቃ) ያጠቃልላል።

- ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ ጠረጴዛዎች እና ወንበሮች መፅዳትና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ መደረግ አለባቸው፣ እንዲሁም የቼክ ፕሬሴንቴርስ ከእያንዳንዱ አገልግሎት በኋላ መፅዳትና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ መደረግ አለባቸው ። የማፅጃ ወይም ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርት ትርፍራፊ በጠረጴዛው ወለል ላይ እንዳልቀረ ያረጋግጡ ።

- የማህበራዊ ርቀት መመሪያዎችን የሚከተሉ መሆናቸውን ለማረጋገጥ መጸዳጃ ቤቶች በየጊዜው መጽዳት እና ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ መደረግ እና በተገቢ ሁኔታ ሊተኮርባቸዉ እና ቁጥጥር ሊደረግባቸው ይገባል ፡፡ በቂ የሆነ የሳሙና እና የእጅ ማድረቂያ ወረቀት አቅርቦት በማንኛውም ጊዜ መኖራቸውን ያረጋግጡ ፡፡
- ሁሉም የምግብ ንክኪ ያላቸዉ ነገሮች ቢያንስ በየ 2 ሰዓት መጸዳት እና ሰኒታይዝድ መደረግ አለባቸው ፡፡ ከሬስቶራንቱ መከፈት ጋር ተያይዞ ውስጥ ያሉት የጽዳት ሂደቶች ሊሻሻሉ እና በትክክል እንዲሠለጠኑም ለሠራተኞች ሊጋሩ ይገባል፡፡
- የእቃ ማጠቢያ ማሽኖች በሚፈለገው መልኩ ማጠባቸዉን እና የማለቅለቂያ ሙቀት እና አግባብነት ያላቸው ሳሙናዎች እና የንፅህና አጠባበቅ ሳኒታይዘር አቅርቦቶች መኖራቸውን ያረጋግጡ ፡፡
- COVID-19 ን የሚያስከትለውን ቫይረስ ለማጥፋት ውጤታማ ስለሆኑ ከበሽታ አምጪ ህዋሳት ነፃ የማድረጊያ ምርቶች ተጨማሪ መረጃ ለማግኘት የ CDC ድረ ገጽ ይመልከቱ cdc.gov/coronavirus/2019-ncov/community/organizations/cleaning-disinfection.html ፡፡

ወረርሽኙ እየተስፋፋ በሄደ ቁጥር ከላይ ያሉት መመሪያዎች እየተሻሻሉ ይሄዳሉ። እባክዎን ለወቅታዊ መረጃ በቋሚነት coronavirus.dc.gov ን ይጎብኙ።